# የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ (ሸንጎ)

**Ethiopian People's Congress for United Struggle (Shengo)**

www.ethioshengo.org shengo.derbiaber@gmail.com

## ለጎንደር ሕብረት ጥሪ የተሰጠ መልስ

ሃምሌ 28 ቀን 2008 ዓ.ም.

በቅድሚያ ባለፈው እሁድ ሃምሌ 24 ቀን 2008 ዓ.ም.በጎንደር ከተማ የተካሄደው ሕዝባዊ ሰላማዊ ሰልፍ ላለፉት ሃያ አምስት ዓመታት በአገራችን በኢትዮጵያ ሰፍኖ የቈየውን ዘረኛ አገዛዝና ስርዓት ለማሶገድ ያሰፈነውን የፍርሃት ድባብ ሰብሮ የወጣ፣የአገራችንን አንድነት ለማስከበር ድፍረትና ወኔ የተላበሰ ፣አገር ወዳድ ስሜት የተንጸባረቀበትና አንገቱን ደፍቶ ለኖረው ሕዝብ የሞራል ንቃቱን የቀሰቀሰ ፣በመሆኑ ልንኮራበት ይገባል።የፖለቲካ ድርጅቶች ማድረግ የሚገባቸውን ሕዝቡ በራሱ አነሳሽነት የፖለቲካም ሆነ የታጠቀ ቡድን ሳይገባበትና ሳይመራው በቃኝ ብሎ ይህን የመሰለ የተቀናጀ፣ስነስርዓት ያለው፣የተቃውሞ ሰልፍ ሲያደርግ ማየት የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይም የጎንደር ሕዝብ ምን ያህል ስነምግባርና ጀግንነት ያለው ለመሆኑ ማረጋገጫ ነው።እንደቀድሞቹ መሪዎቻችን እንደ አጼ ፋሲልና አጼ ቴዎድሮስ የነጻነት ምልክት የሆነችውን ባንዲራችንን ከፍ አድርጎ ለመታገል ለጎንደር ሕዝብ እንግዳ ሳይሆን ባህልና ልማዱ ነው።ሸንጎ ይህን ኩሩ ሕዝብ፣ይህን ለጠላት እጁን የማይሰጥ ሕዝብ ያከብረዋል፣ ይኮራበታልም።ለኢትዮጵያ አንድነት የከፈለውን መስዋዕትነት በማድነቅ አሁን በመክፈልም ላይ ባለው ትግል ከጎኑ መቆሙን ሊያረጋግጥ ይወዳል።

የጎንደር ሕብረት በሰሞኑ ባካሄደው ስብሰባና ባሳለፈው ውሳኔ የፖለቲካ ድርጅቶችና ሌሎቹም የሲቪክ ማህበራት ተባብረው ንቅናቄውን ከሕዝቡ ጋር አብረው ከግቡ እንዲያደርሱ ብሎም የሽግግር መንግሥት ለማቋቋም አብረው እንዲሠሩ ያሳለፈውን ጥሪ በአክብሮት ይቀበላል።

ሸንጎ የተመሰረተበትም ዓላማ የኢትዮጵያን የግዛት አንድነት ፣የሕግ የበላይነት፣የዴሞክራሲ ስርዓት መስፈንን፣የሁሉም ዜጋ መብት የተረጋገጠባትን ኢትዮጵያን ለመፍጠርና ይህን በሥልጣን ላይ የተቀመጠ አገር አጥፊ የጎሳ ስብስብ በጋራ አሶግዶ በምትኩ ሁሉንም ያሳተፈ የሽግግር መንግሥት ለማቋቋ ስለሆነ ከጎንደር ሕዝብ ትግልና ከጎንደር ሕብረት ዓላማ ጋር ይስማማል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ ከጥዋቱ፣ከምስረታው ጀምሮ ጥረት ያደረገውና አሁንም የሚጥረው በኢትዮጵያ አንድነት የሚያምኑትን ሃይሎች ለነደፈው ዓላማ መተግበር በማሰባሰቡ ሥራ ላይ በመሆኑ ፍላጎቱ ፍላጎታችን መሆኑን ለማረጋገጥ ይወዳል።በሸንጎው ውስጥ የተሰባሰቡት የፖለቲካ ድርጅቶች፣የሲቪክ ተቋማትና የታወቁ ግለሰቦች የኢትዮጵያ

ሕዝብ በተለይም የጎንደር ነዋሪና ተወላጅ ከሚያደርገው ትግል ጎን መሰለፋቸውን እያረጋገጡ፣የጎንደር ሕብረት ለዚህ ለተቀደሰ አገር አድን ተልእኮ አብሮን እንዲቆምና በጋራ ልንሰራ በምንችልባቸው አያሌ ዘርፎች በመተባበር ያሳለፈውን የተባበሩ ጥሪ በራሱ እንዲጀምረው እንጠይቃለን።ለዚህም ጊዜ ሳይወስድ የሸንጎና የጎንደር ሕብረት አመራር አካላት በአካል ተገናኝተው ስለሚካሄደው ትግልና አብሮ ለመስራት በሚያስችለው ዙሪያ ውይይት እንዲደረግ ሸንጎ ያሳስባል።

ድር ቢያብር አንበሳ ያስር!!!

የኢትዮጵያ አንድነት፣በአንድነት ሃይሎች ህብረት ይረጋገጣል!

የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ(ሸንጎ)

Tel: 44 7937600756 , +1 9168486790 E-mail : shengo.derbiaber@gmail.com